# አሲምባ ርዕስ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 2/2006


# የሳዑዲ አረቢያ መንግስት በወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለውን ኢሰብአዊ ግድያና ወከባ እያወገዝን ኢትዮጵያዊነት የሚያንገበግበን ወገኖች ግን እንደራጅ! እንደራጅ! እንደራጅ!

ሰሞኑን የሳዑዲ አረቢያ መንግስት በወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለውን ኢሰብአዊ ግድያና ወከባ በዓለም ዙሪያ ያለነውን ኢትዮጵያውያን ስላስቆጣን በየፊናችን እያወገዝን እንገኛለን። በአንድ ድምፅም ልናወግዝ የተገባ ነው። የዚህ ድህረ-ገጽ ዝግጅት ክፍልም የሳዑዲን መንግሥት በጥብቅ ያወግዛል።

ነገር ግን ይህን በወገኖቻችን ላይ በሳዑዲ መንግሥት የደረሰውን ወከባና ግድያ ስናወግዝ ኢትዮጵያውያን የሀገራችንን የፖለቲካ ሁናቴ በጥሞና ልንመረምርና ልንመካከርበት የተገባ ነገር እንዳለ ልንጠቁም እንወዳለን። በሳዑዲ መንግሥት የተደረገው ያበግነናል ሆኖም ግን ከመቼውም የበለጠ ሀገር ወዳዶች ስለኢትዮጵያችን ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለብን።

በሳዑዲ የተፈጠረው የሰሞኑ ሁናቴ ሁላችንም የምናውቀው የተሰደዱ ወገኖቻችን ላይ በየሀገሩ የሚደርስባቸው ግፍና ሰቆቃ ሞትንም ጨምሮ አመላካች ትንሹ ምልክት ነው። ወያኔ በሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ ወገኖቻችን በዘመናዊውና ረቂቁ ባርነት ከቀያቸው እየተፈነገሉ በአቀባባይ ነጋዴዎች ከኢትዮጵያ ጀምሮ በመላው አፍሪቃ በደቡብ በሰሜን፣ ምሥራቅና ምዕራብ ፣ የሰሃራንና የሳይናይን በረሃ፣ የቀይ ባሕርንና የሜድትራንያን ባሕር በሚቀባበሏቸው ጨቃኝ ነጋዴዎች ሊታረዱ እንደሚነዱ የፋሲካ በጎች እየተነዱ ከሞት የተረፉት ምን እንደሚደርስባቸው በየዕለቱ የምንሰማው በኢትዮጵያዊነት ላይ የተነጣጠረ ትልቅ አደጋ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በሕግ ሠራተኞችን ወደ ውጪ እንልካለን የሚሉ ስግብግብ ነጋዴዎችም በወያኔው መንግሥት ቡራኬ በየቀኑ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚጋዙት በሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ወገኖቻችን ከአይሮፕላን ማረፊያው ጀምሮ ፓስፖርቶቻቸውን ተቀምተው በሚደርሱበት ሀገር የነፃ ያክል ለባርነትና ዝሙት እየተቸበቸቡ ለመሆኑ ያደባባይ ሚስጥር ነው። በዓለም ዙሪያ ያለን ኢትዮጵያውያንም ልክ እንደ ሳዑዲ ዓይነት ጎላ ብሎ የሚታይ ሁናቴ ብቻ ሲመጣ የደመ ነፍሳችንን <u>በተናጠል</u> ውጥተን ለአንድ ሰሞን ከመጮህ ባሻገር በዓለም መድረክ ወገኖቻችንን የምንከላከልበት አመርቂና ቀጣይነት ያለው ሥራ ለመሥራት ያስቸገረን ለምንድር ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ያላገኘንለት አሳዛኝ ሁናቴ ላይ እንገኛለን።

ስለ ስደት ካወራን ደግሞ በደርግ ዘመነ መንግሥት ካለ ፍላጎታቸው ከሞት አምልጠው ለስደት ከተዳረጉት ውጪና በዘመነ ወያኔም በፖለቲካ ምክንያት በሚደረግ ግፊትና በምዕራባውያን የማያቋርጥ የሠለጠነ ርካሽ የሰው ጉልበት ፍለጋ እየተካሄደም ባለው ዘመናዊው ባርነት ሀገሪቱን ሊጠቅም የሚችለው የሰለጠነ የሰው ኃይል በፈቃድ ሀገር ለቆ ለመፍለስ የመሽቀዳደሙ በሽታም ያቺን ሀገር የሚጎዳ ትልቁ

ልንመረምረው የሚገባን ሁናቴ ለመሆኑ መጠራጠር አያሻም። እዚህ ሰሜን አሜሪካ እንኳ በተለያዩ ዩኑቨርስቲ ውስጥ የሚያስተምሩ ያፈራች ኢትዮጵያ በሀገር ቤት ያሉ ኮሌጆቻችንና ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚያስተምሩ መምሕራን ከውጪ ከአፍሪካ ሀገሮች ሳይቀር በውድ ዋጋ እያስመጣች እንደሆነ ለሚሰማ ሀገራችን በወያኔ ለውድቀቷ እየተመቻቸች ለመሆኑ ጥርጣሬ ሊገባን አያስፈልግም። ታዳጊ ሕፃናት ሳይቀሩ በጉዲፈቻ ስም (adoption) በወያኔ ባለሥልጣናት በተዋቀሩ የዘመኑ ሀገር ቤትና የምዕራባውያን ነጋዴዎች በይፋ ካለምንም ቁጥጥር በተለያዩ ማታለያዎች ቤተ-ሰቦቻቸውን በማወናበድ ሕፃናት እየተሸጡ ነው። በዚሁ በሰሜን አሜሪካ እንኳ የሚደርስባቸው አደጋ ለጆሮ የሚቀፍ እየሰማንና እያነበብን አሁንም ብዙ ኢትዮጵያውያን ባለንበት ድምፃችን ከፍ አድርገን የምጮኽበት መድረክ አልባ ሆነን የምንኖርበት፣ ነገር ግን ብዙ ችሎታ ያላቸው ሙያተኞች ከሌላው አፍሪካ ሀገሮች ከሚመጡ ሁሉ በእጥፍ በተሰባሰብንበት ዓለም የተበታተንን ሆነን መገኘታችን ይቅርታ የማይደርግለት ትልቁ ድክመታችን ነው። በእርግጥ በኢትዮጵያዊነት የምናምን ሀገር ወዳዶች በተደራጀ መልክ መንቀሳቀስ አለመቻላችን ዋነኛው ምክንያት ወያኔና እኛኑ የሚመስሉ ሀገር ወዳድ ነን የሚሉን ነገር ግን የተለያየ አጀንዳ ያለቸውና ፀረ ኢትዮጵያ ቡድኖች በመካከላችንና በምንሰባሰብባቸው ድርጅቶች፣ የኃይማኖት ተቋሞች ሳይቀር ከውስጥ ሰርገው በመግባት እያመሱን በኢትዮጵያዊው ወገን ከፍተኛ አለመተማመን እንዲነግስ ማድረገቸው ያለንበት ሁናቴ ራሱ ምስክር ቢሆንም፤ ኢትዮጵያውያን ይሄንን ግድብ በጣጥሰን መወጣት ይኖርብናል።

ለዚህ ደግሞ መደራጀት! መደራጀት! መደራጀት! የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። መደራጀት ስንል <u>በኢትዮጵያዊነት</u> አጀንዳ የሚለው ሊሠመርበት ይገባል። ኢትዮጵያውያን እንደራጅ እንሰባሰብ ስንል ደግሞ የግድ በፖለቲካ ፓርቲ ማለትም አይደለም። በኢትዮጵያዊነት የምንተማመን በሙያችን ለምሳሌ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን የሕክምና ባለሙያዎች ማህበር፣ ወይም በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን አርቲስቶች ማኅበር ወይም ደግሞ በዋሺንግተን ከተማ የኢትዮጵያውያን ኮሙኒቲ ማህበር፤ ታክሲ ነጂዎች ማኅበር፤ የኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ማኅበር፤ በሌላም ሌላም መደራጀት ያስፈልገናል። የሃይማኖት ተቋማትም ድርጅቶቻችን ናቸው። በነገራችን ላይ የነዚህ ዓይነት ድርጅቶች መስፋፋት ለፖለቲካ ድርጅቶችና ለዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ማበብ መሠረቶች ናቸው። መሠረታችን ግን የዘር ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባዋል። ፀረ-ኢትዮጵያውያንን እናስደስት ብለን ከመንገዳችን ውጥተን ወይም ገና ለገና አንዳንድ ፖለቲከኞችን ላለማስቀየም በመካከላችን የምናደርገውን ግርግር ማቆም አለብን። ለምሳሌ በሰሜን አሜሪካ ስለ ሀገራችን ሁናቴ ለመወያየት የተጠራ አንድ ስብሰባ ላይ የኦነግ ባንዲራ በመድረኩ ላይ ከኢትዮጵያ ባንዲራ ጎን ካልቆመ የኢትዮጵያ ባንዲራም መውለብለብ የለበትም የሚለውን ዓይነት አማራጭ የማንቀበል መሆናችንን በግልጽ የምናስቀምጥበት ዓይነት የጀርባ አጥንትም ሊኖረን ይገባል ለማለት ነው።

በኢትዮጵያዊነት አጀንዳም እንሰባሰብ ስንል እንደ ኦነግ ካሉ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት ከሚንቀሳቀሱ ጋር በሰሜን አሜሪካ ፍልሚያ እንግጠም ማለትም አይደለም። ማንም ወደደም ጠላም ኢትዮጵያዊነትን እንደሚጋባ ቁምጥና በሽታ የምንሸሸው ሳይሆን እቅፍ የምናደርገው፣ ያውም ባደባባይ ያበጠው ይፈንዳ ብለን አንገታችንን ቀና ፣ ደረታችንን ነፋ አድርገን የምንሄድበት ሁናቴን የምንፈጥርበት መሆን አለበት።

ለዘመኑ የዘረኝነት ወረርሽኝ በሽታም ማርከሻው ኢትዮጵያዊነት ብቻ መሆኑን አውቀን ኢትዮጵያዊነት በሁሉም መስክ እንዲንፀባረቅ ማድረግ፤ መጠየቅም የእያንዳንዳችን ፈንታ መሆን አለበት። በዚህም ዓይነት ስነ-ልቦና የምንገነባው ኢትዮጵያዊነት እንደ አባቶቻችን ከብረት የጠነከረ ዕምነትንና መተማመንን በመካከለችን የምንገነባበት፤ ሰልፍ ውጡ ስንባል በተናጠል ወጥተን የሰለለ ድምፅ አሰምተን መመለስ ሳይሆን በተቀነባበረ መልክ በአንድነት ቀፎው እንደተመታ ተርብ ተናዳፊ ሆነን በመውጣት የዓለምን ሚዲያዎች እስክስታ የምናስመታበትና መልዕክታችን በግልጽ የሚተላለፍበትን ሁናቴ የምናመቻች ኃይላችንን የምናሳይበት መሆን ይገባዋል። ድርጅት ውስጥ ባንገባም እንኳ እንደግፍም ካልን መመዘኛችን የኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ለማጠቃለል፡-

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅሙን የሚያስጠብቅ ተጠናክሮ የወጣ ድርጅት ስላልነበረው በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለት ፀረ-ሕዝብ መንግሥታት ሲወድቁ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ዴሞክራሲያዊ ዕድገት ደንታ የሌላቸው የተደራጁ ኃይሎች በትረ ሥልጣኑን መቀማታቸው የደርግንና የወያኔን አመጣጥ የምናውቅ ብዙዎቻችን የምንመሰክረው ነው። ደርግና ወያኔ የሕዝብ ድጋፍ እንደሌላቸው አስቀድመው ስለሚያውቁ ያሉትን ሕዝባዊ ድርጅቶችን የኃይማኖት ተቋሞችን ሳይቀር በምስላቸው ቀርፀው ማኖር ወይም የሚነዱላቸውን ጀሌዎች በመሪነት በማስቀመጥ ድርጅቶችን የሥርዓቶቻቸው ተቀጢላ ማድረግ ወይም ማፍረስ ካልሆነም በውጥረት እንዲዳከሙ ከሃዲዎችን በሰርጎ ገብነት በመሰግሰግ ማተራመስ ዋና ዘዴዎቻቸው ለመሆኑ ዛሬ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያላቸው ድርጅቶች በዕቅድ የሚደርስባቸውን ወከባና የመከፋፈል ሤራ ለተመለከተ መረዳት አይከብደውም። የሚስገርመው ነገር ደግሞ ሰሞኑን የሳዑዲ አረቢያ መንግስት በወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለውን ኢሰብአዊ ግድያና ወከባ ዓይነት ሁላችንንም የሚያስቆጣ ሁናቴ በሚፈጠርበት ጊዜ አዛኝ የቂቤ አንጓቾች መሪ ነን ባዮች ከየተደበቁበት ብቅ ብለው ሁናታው የወያኔን ሥርዓት በሚያስመታ አቅጣጫ እንዳይጓዝና እንቅስቃሴዎ እንዲቀጭጭ ወይም እንዲሞት ለማድረግ በስሜት የተነሳሳው ህብረተሰብ ክፍል የተደራጀ እንቅስቃሴ የመጀመር አዝማሚያ በድንገት እንኳን ከማምጣቱ አስቀድመው እንዲለሳለስና እንዲበታተን የሚያደርጉ የመሪነቱን ቦታ ለመያዝ የሚሽቀዳደሙ፤ እንዲያውም አዲስ ድርጅት ሳይቀር ፈጥረው ከጥቂት ጊዜ በኋላ የውሃ ሽታ ሆነው የሚጠፉ ተቀጣሪዎች ለመኖራቸው እሩቅ ሳንሄድ የወያኔ መንግሥት የምዕራብ ኢትዮጵያን ቆርሶ ለሱዳን መንግሥት በሰጠበት ጊዜ የቦርደር ኮሚሽን በማለት ብቅ ብለው የነበሩት በቀጣይነት የሠሩትን ብንመለከት ምንም አለመሆኑን እንደ አንድ ምሳሌ ልንጠቅስ የምንችለብት ዓይነት ወያኔ የሚሠራብን መሆኑንም መረዳት ይኖርብናል።

ስለሆነም መደራጀት! መደራጀት! መደራጀት! ስንል ድርጅቶችን ኢትዮጵያዊነት አጀንዳና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በታኞች በመካከላችን ገብተው ሊያተራምሱበት የሚችሉበትን ቀዳዳ ሁሉ መድፈን አንደኛው ልንመረምረው የሚገባ ነው። ለዚህ ደግሞ የምንፈጥራቸው ድርጅቶች ውስጥ ግልጽነትና የሕግ የበላይነት እንዲኖር የመተዳደሪያ ደንቦቻችን የግንኙነት መሠረቶቻችን፤ ዕርስ በዕርስ የሚያካስሱ ሁኔቴዎችም ቢመጡም በስሜት ወይም በሃሜታ ጋጋታ ከመነዳትና ፈራጆች ከመሆን በፊት የከሳሹም ሆነ የተከሳሹ ድምጽ እኩል በጊዜው ባለው የመተዳደሪያ ደንብ ተመሥርቶ በጥንቃቄ ዕውነቱን ከውሸቱ ማበራየት በፈረንጅኛውም (due process) ሊኖረን ይገባል እንላለን።

ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እንደራጅ! እንደራንጅ! እንደራጅ!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል

አስተያየቶን Webmaster@Assimba.org ብለው ይላኩልን